የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የቀረበ አገራዊ ጥሪ

## <u>የግንቦት ምዕራፍ አልተዘጋም፥ አይዘጋም!!</u>

የግንቦትን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ድሎች የማስከበሩ ጉዳይ የዚህ ወይም የዚያ ድርጅት፥ የዚህ ወይም የዚያ ቡድን ወይም ግለሰብ ሳይሆን በጠቅላላው በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና በእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት ትከሻ ላይ የወደቀ ታሪካዊ ተልእኮ ነው፡፡ በዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ እኛ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ሥር ተደራጅተን የምንታገል ዴሞክራቶችና አገር-ወዳዶች ኅብረታችን "ዜጎች ለግንቦት ድሎች ይሰባሰቡ" በሚል ያቀረበውን አገራዊ ጥሪ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ተቀብለው በያሉበት የሕዝባችንን ድል ለማስከበር ዘብ መቆማቸውን ተመልክተን በዚች አገርና በሕዝባችን ያለንን እምነት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ እንዲጎለብት አድርጎታል፡፡

ሆኖም ለዚች አገራችን ዘብ እንድትቆሙ ጥሪ ያደረግንላችሁ ወገኖቻችን ከቅርብ ሳምንታት ወዲህ በተፈጠሩ ውዥንብሮች ምክንያት ትግሉ ከላይ ሲታይ የመንገዳገድ መሰል ሁኔታን በማንጸባረቁ እንደኛው ከፍተኛ ጭንቀትና አሳብ ላይ እንደምትገኙ እየተገነዘብን ነው፡፡ በእኛ ግምት ዛሬ የምንገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ያደረሱን ድክመቶች ባስቸኳይ ታርመው ለዚህ ተጋድሎአችን አዲስ እስትንፋስ የመስጠቱን ጉዳይ የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገን ስለምንወስደው ስለ ቀጣዩ ትግል የሚታየንን አቅጣጫ ለወገኖቻችን ለማካፈል እንወዳለን፡፡ ዋናው መልእክታችን ከወዲሁ ግልጽ ይሁን፥ የግንቦት ምዕራፍ አልተዘጋም፥ አይዘጋም፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት ሕዝባችን እየተነጠቁ ያሉትን ታሪካዊ ድሎች በተረጋገጠ መልክ መልሶ እጁ ውስጥ ለማስገባት የሚያደርገው ትግል ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሞታል፡፡ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎበታል፡፡ ሆኖም የተከፈለውን መስዋዕትነት በሚመጥንና <u>"ድል አይቀሬ ነው"</u> ብለን አፍ ሞልተን ለመናገር በሚያስችል መልክ ትግላችን ሥር እንዲሰድ፥ እንዲሰፋና እንዲቀነባበር ካላደረግን የግንቦት ድሎች እንደተነጠቁ ቀርተው አገራችንና ሕዝባችን አንቅረው ወደተፉት አስከፊ ሥርዓት ተመልሰው የሚዘፈቁበት አደገኛ ሁኔታ ከፊታችን ተደቅኗል፡፡ ይኸ ውድቀት ከመጣ የሚያስከትለውን ውጤት የኢሕአዴግ መሪዎችን እብሪትና ፀረ-ሕዝብነት የሚያውቅ ዜጋ ሁሉ የሚስተው አይመስለንም፡፡ ከአዲስ አበባ አንስቶ በየክልሉ በያለበት በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ታጋይ ዜጎች ከኢሕአዴግ ካድሬዎችና ከመንግሥት ባለሥልጣናት እየተፋጠጡና እየተጋፈጡ፥ ገና ያልበረደላቸውን እብሪት እየተቋቋሙ ያቀጣጠሉት ትግል ሽንፈት ቢያጋጥመው እነዚህ ዜጎቻችን ለአስከፊ የአፈና ውርጅብኝ እንደሚጋለጡ ማንም ብዥታ ሊኖረው አይገባም፡፡

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር(Tel.No) 2511-574719;(Fax) 2511574720

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

በዚህ መልክ እነዚህ በትግላቸው ገፍተው ድል ከማድረግ ሌላ ምንም አማራጭ የሌላቸው ግንባር ቀደም ዜጎቻችን በሚጠይቁት መሠረት የዚህን ታሪካዊ ተጋድሎ አመራር ወድደንና ፈቅደን የተቀበልን ወገኖች በአንድ በኩል ለትግሉ ጥራትና አቅጣጫ እየሰጠን ታግለን የማታገል በሌላ በኩል ደግሞ በያለበት በትግሉ ካገኙት ተመክሮ፥ በያለበት የሕዝባችንን የልብ ትርታ እያዳመጡ የሚያቀርቧቸውን አሳቦች እኛም የማዳመጥ ግዴታ እንዳለብን እንገነዘባለን። በመሆኑም በያለበት ላላችሁ ታጋይ ዜጎች ኅብረታችን ዛሬ እየተከተለ ካለው አላፊና ጠፊ ውዥንብር ባሻገር የተያያዛችሁት የግንቦትን ድሎች የማስከበር ተጋድሎ እየሰፉ፥ እየተቀነባበረና እያየለ ሄዶ ለአይቀሬው ሕዝባዊ ድል እንዲበቃ ከድርሻችን በላይም ቢሆን አስተዋጽዖ ለማድረግና ከእናንተና ከሕዝባችን ጋር ለድል ለመብቃት ያለንን ቁርጠኛነት እናረጋግጥላችኋለን።
ለዚህ ደግሞ በሚቀጥሉት ቀናትና ሳምንታት መከተል ስለሚኖርብን የትግል አቅጣጫ ያለንን አሳብ ከመሰንዘራችን በፊት ኅብረቱን በወቅቱ ሊቀ-መንበርነትና ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ-መንበርነት ሲያገለግሉ የቆዩት ሁለት አባላት የብዙሃኑን ውሳኔ ጥሰው በኢሕአዴግ ፓርላማ በመግባታቸው ሳቢያ ስለተፈጠረው ቀውስ ያለንን አስተሳሰብ ለማካፈል እንፈልጋለን።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ወደዚህ ፓርላማ መግባት የለብንም የሚለው ውሳኔ ላይ የደረሰው በጥቂት የኅብረቱ አባል ድርጅቶች አይደለም፤ ድንገት የተወሰደ አቋምም አይደለም። የኅብረቱ ተወዳዳሪዎች ከሦስት ወራት በፊት ከመላ አገሪቱ ተሰባስበው በአዲስ አበባ ባደረጉት ጉባዔ፥ ከዚያም ለመስከረም ፳ እና ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ታስቦ ለነበረው "የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ" ላይ ለመሳተፍ አዲስ አበባ ተገኝተው የነበሩት የኅብረቱ ታጋዮች በአመዛኙ ያንፀባረቁት ሕዝባዊና ትክክለኛ አቋም ነው። ይኽ ተቃውሞ የሚመነጨው በፓርላማው መከፈት ቀን ጀምሮ የተንጸባረቀውን የተሳትፎ ፋይዳ ቢስነት በማጤን ብቻ ሳይሆን መሳተፉ (መግባቱ) የሚያስከትላቸውን መዘዞች በመፍራትም ነበር። ዛሬ እነዚህ መዘዞች አፍጥጠውና አግጥጠው ተከስተዋል። ሆኖም በትግላችን ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ችግሮች በብስለትና በቆራጥነት መዋጋት ይኖርብናል። ይኽ ደግሞ አንድ ነገር ብቻ ማለት ነው። ሰባ ሰባት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጀርባው አሰልፎ በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ሃብታቸውን፥ ጉልበታቸውን መጻኢ ዕድላቸውንና አስፈላጊ ሲሆን ሕይወታቸውን እየለገሱ በማካሄድ ላይ ያሉት ግንቦት የወለደው ታሪካዊ ተጋድሎ አምሳም ሆነ መቶ ወይም መቶ አምሳ ሌሎች ዜጎች እዚህ ሕገ-ወጥ ፓርላማ በመግባታቸው ምክንያት ምንም ዓይነት አሉታዊ ጫና እንዳይኖረው እየተጠነቀቅን ወደፊት ጉዞአችንን መቀጠል አለብን፥ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ቁርጠኝነት እንቀጥላለን ማለት ብቻ ነው።

ከዚህ በመነሳት የኅብረቱን ውሳኔ ጥሰው ፓርላማ በገቡና በቀሩት ታጋዮች መኻከል ኢሕአዴግ እንደሚመኘው የሰፋ ክፍፍል እንዳይኖር ሁሉም ወገኖች በከፍተኛ ጥንቃቄ የመራመድ ሃላፊነትና ግዴታ እንደሚኖርባቸው ተገንዝቦ መንቀሳቀስ ብቻ አይደለም ከዚያም አልፈን በተወሰኑ ዜጎች በተወሰደ በዚህ እርምጃ የኢሕአዴግ መሪዎች በፕሮፖጋንዳው፥ በፖለቲካውና በዲፕሎማሲው መስክ ሊቃርሙ የሚራወጡበትን ሁኔታ የተሻለ ጥራት ባለው ዘዴ ትግላችንን አፋፍመን ልንቋቋመው ይገባል ማለት ነው።

የኢሕአዴግ መሪዎች በተወሰኑ ዜጎች ፓርላማ ውስጥ መግባት ሳቢያ የግንቦቱ ምርጫ ፋይል ተዘግቷል ሊሉን ይቃጣቸዋል። እኛ ደግሞ ሕዝባችንን ከዳር እስከ ዳር በማሰለፍ ለግንቦት ድሎች የሚካሄደው ተጋድሎ ገና የሚቀጥልና የሚፋፋም መሆኑን ልናረጋግጥላቸው ይገባል። የኢሕአዴግ መሪዎች ከፓርላማ ውጭ የሚካሄደውን ትግል "ሕገ-ወጥ" አርገው በአመፅ ለመደምሰስ ላይ ታች ሊሉ ይችላሉ። እኛ ደግሞ ሌላው ቀርቶ ከራሱ ከኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት አንፃር ሕገ-ወጡ ይኽ የድምፅ ሌቦች ዋሻ የሆነው ፓርላማ መሆኑን ለማሳየት ያላሰለሰ ትግል ማካሄድ ይኖርብናል። የኢሕአዴግ መሪዎች ቀጣዩንና አይቀሬውን ትግል የጥቂቶች ሴራና አጉል መፍጨርጨር አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። እኛ ደግሞ

"ጥቂቶቹ" እነሱ እንጅ የእኛ ተጋድሎ አንድ ሕዝብ በነቂስ አሻፈረኝ ብሎ የሚንቀሳቀስበት ማዕበል መሆኑን በተግባር ማሳየት ይጠበቅብናል። ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ የተባለውም እራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ሕልም የማይመጥንና ዓለም-አቀፍ መስፈርቶችን አያሟላም ብሎ ያጣጣለውን ሂደት እዛው በዛው በአንድ እራስ ሁለት ምላስ በመሆን "ለእናንተ ያህል ይበቃል" በሚል ንቀት የተወሰኑ ዜጎች ፓርላማ በመግባታቸው ብቻ ሕዝቡም ድምፁ በታፈነበትና በተሰረቀበት ሁኔታ የምርጫ "ውጤቱን" እንዲቀበል አንዳንድ ግፊት እያደረገ መሆኑን እናውቃለን። ይኽንን ግፊት ከአገራችን ያለፈ ታሪክ፥ ዛሬ ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታና ለነገይቱ ኢትዮጵያችን ካለን ሕልም እየተነሳን የሰላማዊ ትግል ስትራቴጂ የመቀየሱን ሃላፊነት ለእኛ ለአገሪቱ ታጋይ ኃይሎች እንዲተውትና እነሱ ለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን እራሳችን ለራሳችን ለምናደርገው ለሰላማዊና ሕጋዊ የዴሞክራሲ ትግል በአጋዥነት ብቻ እንዲሰለፉ ለማሳሰብና ታጋይ ሕዝባችን በዴሞክራሲ ፍርፋሪ እንደማይረካ ለማሳየት ከዳር እስከ ዳር "ዜጎች ለግንቦት ትግሎች" ብለን በአንድ ልብና በአዲስ ወኔ መነሳት ይኖርብናል።

ይኽንን ስንል አሁንም ዓላማችን ምን እንደሆነ በግልፅ እናስቀምጣለን። የእኛም ሆነ የጠቅላላው ኅብረተሰባችን የትግል ዓላማ በግንቦት ሰባት ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም በሕዝብ ደምና መስዋዕትነት ተገኝተው የነበሩትንና ዛሬ በኢሕአዴግ በመነጠቅ ላይ ያሉትን ድሎች የማስመለስን ያህል ክቡር የሆነ አገራዊ ዓላማ ነው። ለዚህ ደግሞ አንድ ሽህ አንድ ትርጉም የለውም። የሕዝባችን ድምፅ ተከብሮ የግንቦትን የሰላም፥ የዴሞክራሲና የብሔራዊ እርቅ ድሎች ለማጎልበት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ እንዋደቅ ማለት ነው። የትግሉ ስልትም ለእኛ ከፀሐይ ብርሃን የበለጠ ወለል ብሎ በግልጽ ይታየናል። ሕዝባችን መዋደቁና መሰዋቱ ሳይቀር አሁን እንደሚታየው በያለበትና በስንጥር ተራ በተራ እየተነሳ በያለበትና ተራ በተራ እየተመታ ወደ አስከፊ ውድቀት እንዳይነጉድ <u>በአገር-አቀፍ ደረጃ ሁሉም እጅ ለእጅ ተያይዞ እንዲራመድ እንጥራለን።</u>

ከዚህ አንፃር ሲታይ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት በአንድ በኩል ለትግሉ ቀጣይነትና ቅንብር ሲባል የሚወሰኑ አንደ አገር-አቀፍ የታጋዮች ጉባዔ ዓይነት የትግል ቀጠሮዎች ተፈጻሚነት በማጣታቸው በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ትግል ውስጥ ወሳኝ የሆነውን ሕዝባዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የተነደፉ እቅዶች ለሕዝቡና ለታጋዮች በሚሰጡ የትግል ጥሪ ዥዋዥዌዎች ምክንያት ተግባራዊ ባለመሆናቸው ኅብረተሰባችን ለቅልበሳ በሚመች አደገኛ ውዥንብር ውስጥ እንዲወድቅ ተደርጓል። ከዚህ ችግር ወጥተን ወደ አስተማማኝ ድል የሚመራንን አቅጣጫ ለመያዝ በመነጠቅ ላይ ያሉትን የግንቦት ድሎች መልሶ ሕዝባችን እጅ ለማስገባት የሚደረገው ትግል ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የሲቪኩ ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ስብስብ መሪዎች እንዲሁም በአጠቃላይ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ዜጎች በአስቸኳይ በሦስት ቁም ነገሮች ተስማምተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

<u>አንደኛ</u> ፦ በሚቀጥሉት ቀናት ዜጎች ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው በአንድ ድምፅ የሚንቀሳቀሱበት ግልፅ <u>የጋራ አጀንዳ</u> ስለማስፈለጉ፤

ይኽንን የጋራ አጀንዳ የመጠቆሙ ጉዳይ በቅድሚያ በትግሉ መስክ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ በመሆኑ አሁን ባሉት በሁለት ዋና ዋና ተቃዋሚ ድርጅቶች ማለትም በቅንጅቱና በኅብረቱ መኻል በዚህ ጉዳይ የሚንፀባረቁት የጭብጥም ባይሆን የትኩረት ልዩነቶች ተጣጥመው አንድ የጋራ የትግል አጀንዳ የሚይዙበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል።

ሕዝባችን ለታጋይ መሪዎቹ የሰጠው አደራና ተልዕኮ ምንም በማያሻማ ሁኔታ ግልጽ ነው። እሱም የተሰረቀ ድሌን ለማስመለስ በማደርገው ትግል <u>አመራር ስጡኝ</u> የሚል ጥሪ ነው። ኅብረታችን ለዚህ የሕዝብ ጥሪ መልስ በመስጠት ባለፈው መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፰

ዓ/ም “ዜጎች ለግንቦት ድሎች” ብለን እንሰባሰብ በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ የምር ትኩረት የሚሰጠው ለዚህ ዓላማ መሆኑን በማስረገጥ በሰባት ነጥቦች ዙሪያ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ጥሪ አቅርቧል፡፡ የቅንጅት የትግል አጋር ወገኖቻችን በበኩላቸው የድርጅቱ ተመራጮች ፓርላማ እንዲገቡ ከተፈለገ መሟላት አለባቸው የሚሏቸውን ስምንት ቅድመ-ሁኔታዎች አስቀምጠው ኢሕአዴግ ተደራድሮ እነዚህን ነጥቦች እንዲያሟላ ጥሪ አድርገዋል፡፡ ለትግሉ ጥራትና አንድነት ሲባል ይኸ ክፍተት በአስቸኳይ ተደፍኖ ከስምንቱ የቅንጅት ነጥቦችና ከሰባቱ የኅብረት ነጥቦች ተውጣጥቶም ቢሆን ዋናው ነገር ለሕዝቡ ድል መከበር ቅድሚያ በሚሰጥ ሁኔታ አንድ የጋራ አጀንዳ (የተግባር እቅድ) እንዲነደፍ ደጋፊዎቻችንንና አባሎቻችን ከነሱም ባሻገር የግንቦት ድል ጉዳይ ያገባናል የሚሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ሁሉ አንድነታቸውን አጠንክረው እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

**ሁለተኛ፡- በሚቀጥሉት ቀናት ከድርድር ይልቅ ለሕዝባዊ ትግል ልዩና አስቸኳይ ትኩረት ሰጥተን በጋራ መንቀሳቀስ ስለማስፈለጉ፤**

ሕዝባችንን ሳንይዝ ባዕዳን ኃያላን በርቱ ግፉ ስላሉን ብቻ ከኢሕአዴግ ጋር የሚሞከር ማንኛውም ድርድር የትም እንደማያደርስ ሌላው ቢቀር የቤት መዋሉን የክተት አድማ ለማሰረዝ ብቻ ኢሕአዴግ የቃጣውንና ይኸን ተልዕኮውን ከፈጸመ በኋላ ወዲያውኑ የተቋረጠውን ድርድር ተብየ ትያትር ማስታወስ ብቻ ይበቃል፡፡ በኅብረቱ ሁለተኛ መደበኛ የሸንጎ ጉባዔ ውሳኔዎች ላይ በትክክል እንዳስቀመጥነው በሕዝብ ትግል ያልታጀበ ድርድር የትም እንደማያደርስ ስለምንረዳ በዚህም ጉዳይ ተቃዋሚ ኃይሎች አንድ የጋራ አካሄድ መንደፍ ይኖርባቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በኩል ሕዝባችን ካልገባበትና የሱም ግልጽ ተሳትፎ በሌለበት ድርድር ምንም አይገኝም ብቻ ሳይሆን በአደራዳሪዎች ግፊት የሕዝቡ ድምፅ ይከበር ከሚለው ዓላማችን አንፃር እዚህ ግቡ የማይባሉ አንዳንድ ውጤቶች ከኢሕአዴግ እጅ መፈልቀቅ ቢቻልም እንኳ ለተፈጻሚነታቸው ምንም ዋስትና እንደማይኖር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ በመሆኑም የጋራ እንቅስቃሴ ስንል በውጭም በውስጥም ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር የግንቦት ድሎችን መከበር ዓብይ ብሔራዊ ጉዳይ በግንባር ቀደምነት አንስተው በቤት መዋልና በሌሎች ሰላማዊ የትግል ስልቶች በመጠቀም በቅድሚያ ሕዝባችንን የትግላችን ዋና ተዋናይ እንዲያደርጉና የኢሕአዴግ መሪዎችን ትርጉም ወዳለውና ፍሬ ወደሚሰጥ ድርድር እንዲመጡ እናስገድዳቸው ማለት ስለሆነ አባሎቻችን፥ ደጋፊዎቻችንና የግንቦት ድሎች መከበር ያገባናል የሚሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ሁሉ አንድነታቸውን አጠንክረው “ከድርድር ሕዝባዊ ትግል ይቅደም” ብለው እንዲነሱ አገራዊ ጥሪያችንን በአክብሮት እናስተላልፋለን፡፡

**ሦስተኛ፡- ለጋራ ትግላችን አገር-አቀፍ መሠረትና ቅንብር ለማጎናጸፍ አስቸኳይ አገር-አቀፍ የታጋዮች ጉባዔ ስለ መጥራት፤**

ቅንጅቱና ኅብረቱ የጠሩት፥ ለትግሉ አዲስ እምርታ ማግኘትና ለአገር-አቀፉ ቅንብር ወሳኝ ነው ብለን የገመትነውና ለመስከረም ፳ እና ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ታስቦ የነበረው በያለበት በመዋደቅ ላይ ያሉ ታጋይ ዜጎችን የሚያካትት “የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ” አዳራሽ አልተገኘም ተብሎ እንዲሰረዝ መደረጉ ይታወሳል፡፡ ስለ ዴሞክራሲና ስለ ዜጎች ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ሌት ተቀን የሚያቅራሩት የኢሕአዴግ መሪዎች በአዳራሽ የመሰብሰብን ያህል መሠረታዊም ቀላልም የሆነ መብት እስከ ማገድ ቢሄዱና በዚህም ቢያንስ በአሳዳሪዎቻቸው ፊት መጋለጥን ቢመርጡ ለዚህ ሊኖር የሚችለው አንድ ምክንያት ብቻ ነው፡፡ ትግሉ ከጥቂት መሪዎች ሰፍቶ በመላ አገሪቱ በመዋደቅ ላይ ባሉ ዜጎች በተነደፈ ስትራቴጅ መመራቱ፥ ትግሉ አንዱ ለሌላው ጀርባውን ሰጥቶ ሁሉም በየፊናውና በተበተነ መልኩ የሚያካሂደው መሆኑ ቀርቶ በአገር-አቀፍ ደረጃ የተቀነባበረ መሆኑ ለእነሱ የሞት ሽረት ጥያቄ መስሎ ስለታያቸው

ነው፡፡ እኛም ነገ ሽንፈት ቢመጣ የአስከፊ አፈናውን ገፈት የሚቀምሱትንና የሚጋፈጡትን የለውጥና የዴሞክራሲ አርበኛ ታጋይ ዜጎች ሰብስበን ከሕዝብ የልብ ትርታና ከትግል ተመክሯቸው የሚፈልቅ አገር-አቀፍ ስትራቴጅ የማውጣቱን ጉዳይ እንደ ኢሕአዴግ መሪዎች የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገን መውሰድ ይኖርብናል፡፡ በመሆኑም ይኽንን አገር-አቀፍ ጉባዔ እንደገና መጥራትና አሁን ግን ቁርጠኝነቱ ኖሮ ኢሕአዴግ የአዳራሽ ስብሰባ እስከ መከልከል ዘልቆ የዜግነት መብታችንን ከነፈገን ካስፈለገ ድንኳን ተክለን ይኸ ባይቻል ደግሞ ሜዳ ላይ ተሰብስበን ጉባዔውን ማካሄድና ለመላው ዓለም የኢሕአዴግ ዴሞክራሲ የአዳራሽ ጉባዔን እንኳን የማይፈቅድ የወስላቶች ልፈፋ መሆኑን ማጋለጥ ይቻላል ብለን ስለምናምን አባሎቻችን፥ ደጋፊዎቻችንና የግንቦት ድል ያገባናል የሚሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችና ዜጎች ለዚህ ጉባዔ እውንነት በቁርጠኝነት ከልብ እንዲንቀሳቀሱ ጥሪያችንን በአክብሮት እናስተላልፋለን፡፡

በመጨረሻም በየድርጅቶቻችን በሚከሰቱ ጊዜአዊ እክሎችም ሆነ ገዥው አካል በሚወስዳቸው የተስፋ መቁረጥና የመወራጨት አሉታዊ እርምጃዎች እንዲሁም ሁሉም ነገር እንዳለቀና እንዳከተመ ለማስመሰል በሚያደርጋቸው መራዎጦች መደናገርም ይሁን በአይቀሬው የሕዝባችን የጋራ ድል ላይ ያለን ተስፋ ሊቀንስ ከቶውንም አይገባም፡፡ እንዲያውም ካለፉ ስህተቶችና ግድፈቶች ትምሕርት ቀስመን የበለጠ እንድንጠነክርና በተሻለና በብቃት ተደራጅተን የግንቦት ድሎችን በአስተማማኝ የሚያስከብር ቁርጠኛና ጥራት ያለው አመራር እንዲሰጥ የተቻለው ሁሉ እንደሚደረግ ለታጋዩና ቆራጡ የተከበረ ሕዝባችን በትህትና እንገልጻለን፡፡

ዜጎች ለግንቦት ድሎች ብለን እንሰባሰብ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ሰላማዊ ትግሉ የተነጠቀ መብቱን ያስከብራል!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰